# አሸባሪነት የወንጀለኛ መንግስት አይነተኛ ባህሪ ነው
ከጋሻ ለኢትዮጵያ የተሰጠ መግለጫ።

ስልጣን ከጨበጠበት ከ1991 ዓ.ም. ጀምሮ የመለስ ዜናዊ ገዢ ቡድን ኢትዮጵያን እንደጠላት ሀገር ሲዋጋ ቆይቷል። በልጆችዋ ከፍተኛ ተጋድሎ ቀይ ባህርን የተፈጥሮ ድንበርዋ አድርጋ የቆየችው ሀገር በመለስ ዜናዊ የህወሓት/ኢህአዴግ መሪነት ወደብ አልባ ሆናለች።

ኢትዮጵያ ከደረሰባት የኢኮኖሚና የፖለቲካ ክስረት ለመታደግ ሲሉ እራሱ ወያኔ ባረቀቀው ህገ-መንግስት ስር ተደራጅተው ዜጎች ለመንቀሳቀስ ቢሞክሩም ገና ከጅምሩ በጠላት እየተመቱ ከስመው ቀርተዋል። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችም በተለያዩ ጊዜያት በሀገሪቱ የነገሰውን ፀረ-ዲሞክራሲና በአጠቃላይ ፀረ-ሀገር ስርአት በሰላማዊ መንገድ ተቃውሟቸውን ለመግለፅ ቢሞክሩም በስርአቱ የፀጥታ ሀይሎች ሰለባ ሆነው ቀርተዋል።

ቀደም ባሉ አመታት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች፣ ማለትም በኦሮምያ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ክልል እንዲሁም በኦጋዴን መንግስት በርካታ ወንጀሎች የፈፀመ ሲሆን፣ ይበልጥ ግን የገዢው ፓርቲ ማንነት ፈጦ የወጣው ከምርጫ 97 በኋላ ነው። ሆ ብሎ የተነሳው የታቃዋሚ ደጋፊን ለማፈን በትንሹ 193 ሰዎች በመለስ የፀጥታ ኃይሎች የተገደሉ ሲሆን፣ በብዙ አስር ሺ የሚቆጠር ህዝብ ደግሞ በአምስት ግዙፍ የማጎሪያ ካምፖች (Concentration Camps) ታፍነው መሰቃየታቸውና አያሌ ታሳሪዎችም በረሀብና በህመም መሞታቸው ይታወቃል።

ይህ ኢትዮጵያን ሲያፈራርስ እና በረሀብ አለንጋ ሲቀጣ የቆየው ቅጥረኛ መንግስት በሀገሪቱ የነበሩት የሙያ ማህበራትን አውድሞ በራሱ አሻንጉሊት ድርጅቶች እየተካ ኖሯል። በዚህ መልክ የወደሙት የቀድሞው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር እንዲሁም የኢትዮጵያ ነፃ ጋዜጠኞች ማህበር ይገኙበታል። እነዚህ የሲቪክ ህበረተሰብ ቋሚ እምዶችና መከታዎች የነበሩት መውደማቸው ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ ለከፋ የባእድ አገዛዝ እንዲጋለጥ አድርጎታል። በሰበቡም በርካታ የአገሪቱ ባለሙያዎች ወይ ለግድያ፣ አልያም ለእስራትና ለስደት ተዳርገዋል።

እንግዲህ ሲቪኩ ህበረተሰብ ነፃነቱን አጥቶ እጅግ በተዳከመበት ሁኔታ ላይ እያለ ነው በላፉት ሳምንታት አሸባሪዎች ናቸው እያለ ነፃ ጋዜጠኞችን እና የተቃዋሚ ፖርቲ መሪዎችን እንዳዲስ ወደ እስር ቤት መወርወር የጀመረው።

አቶ አልባና ሌሊሳና በቀለ ገርባ እንዲሁም ደበበ እሸቱ፣ አንዱ ዓለም አራጌ፣ ዘመኑ ሞላ፣ ናትናኤል መኮንን ከጋዜጠኞችም እስክንደር ነጋ፣ ርእዮት ዓለሙ፣ ውብሸት ታዬና ስለሺ ሀጎስን በአሸባሪነት ወንጀል ተከሰው በእስር ቤት ይማቅቃሉ። እንግዲህ እነዚህ ንጹሐን ዜጎች በአሸባሪነት ከተከሰሱ ቅጥረኛው መንግስት የኢትዮጵያ ህዝብን የሚያየው እንደ አሸባሪ ህዝብ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።

እነዚህ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በሀገሪቱ እንዲሰፍኑ በሰላማዊ መንገድ ሲንቀሳቀሱ የነበሩትን ዜጎች እስሮ እያሰቃየ ያለው ወንጀለኛው ገዢ ፓርቲን ጋሻ ለኢትዮጵያ አጥብቆ ያወግዛል። የመለስ ቡድን በየጊዜው በንጹሃን ዜጎች ላይ እያደረሰ ያለውን ሰቆቃ ማቆም እንዳለበት እየጠየቀ እስከሁን በእስር የሚገኙትንም በአስቸኳይ እንዲፈታቸው ጋሻ ይጠይቃል።

በረሀብ ለተጠቃው ወገን የመጣውን የእህል እርዳታ ሳይቀር እንደመጨቆኛ መሳሪያ እንደሚጠቀም የቢቢሲ ጋዜጠኞች ሳይቀሩ ያጋለጡት ቅጥረኛ ቡድን በኢትዮጵያውያን ላይ እያደረሰ ያለውን ዘርፈ ብዙ ስቃይና እንግልት በአለም ዙርያ የሚገኙ የፍትህ ወዳጆችና ወገኖች እንዲያወግዙትና ብሎም ሰቆቃ እየተፈፀመባቸው የሚገኙትን፣ ራሳቸውን በአርአያነት ያቀረቡትን ብርቅ ሰዎች እንዲታደጋቸው ጋሻ ለኢትዮጵያ ጥሪውን ያቀርባል።

ለመፈታታቸው የሚረዳ ማንኛውንም እንቅስቃሴ እንደ ሰላማዊ ሰልፍ፣ የዲፕሎማሲ ሥራ፣ ገንዘብ አሰባስቦ ዘመዶቻቸውን መጦርና የመሳሰሉትን ሰብአዊ ጉዳዮች ላይ አተኩሮ ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንዲተባበራቸው ጋሻ የበኩሉን ጥሪ ያስተላልፋል። ይህ ነግበኔ የሆነውን ሁኔታና ጊዜ በረዘመ ቁጥር እንደ ሰደድ እሣት የሁሉም ቤት በእየተራ እያዳረሰ የሚገኘው መጠን የሌለው ግፍ ኢትዮጵያውያን ተባብረው እንዲያቆሙት ጋሻ ተጨማሪ ጥሪውን ያቀርባል።

በአርአያነት ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡትን ጠንካራ ዜጎች ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሊቆምላቸውና አስፈላጊዊን ትብብር እንዲያደርግላቸው ጋሻ በድጋሚ ማስታወስ ይፈልጋል።

ኢትዮጵያውያን ከደረሰባቸው ብሄራዊ ውርደት ተላቀው በሀገራችው ዘላቂ ዲሞክራሲ፣ ፍትህ እና የህግ የበላይነት እንዲሰፍን በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ያለውን ጥቃቅን ልዩነቶችን አስወግደው፣ በአንድነት ፀንተው በመቆም ኢትዮጵያን እያፈራረሰ ያለውን ቅጥረኛ ቡድን ከስልጣን ማስወገድ አለባቸው በማለት ጋሻ ጥሪውን ያቀርባል።

የኢትዮጵያ ህዝብ አሸናፊ ነው!

ጋሻ ለኢትዮጵያውያን
መስከረም 2011
ሲያትል ዋሽንግተን